የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 44
ADDIS ABABA, 15th May, 2025


**ማውጫ**


ደንብ ቁጥር ፭፻፸፪/፪ሺ፲፯

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ………………. ገጽ ፲፰ሺ፫፻፹፱


**Content**


Regulation No. 572/2025

Fee Rates Payable for Service provided by Transport and Logistics Minister Council of Ministers Regulation …………Page 18389


**ደንብ ቁጥር ፭፻፸፪/፪ሺ፲፯**

**የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፭ እና በፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ አንቀጽ ፲፯(፩) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፸፪/፪ሺ፲፯” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ድንብ ውስጥ፡-

፩/ “**አዋጅ**“ ማለት የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸፬/፪ሺ፲፬ ነው፡፡

**Regulation No. 572/2025**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR FEES PAYABLE FOR SERVICES PROVIDED BY MINISTRY OF TRANSPORT AND LOGISTICS**

This Regulation is issued by the Council of Miniseters persuant to Article 5 of Definition of Powers and Duties of the Excecutive Organs of Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.1263/2021 and Article 17(1) of Federal Government Financial Administration Proclamation No.648/2009.

1. **Short title**

This Regulation may be cited as the “Fee Rates Payable for Service provided by Transport and Logistics Minister Council of Ministers Regulation No. 572/2025”.

2. **Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means Road Transport Proclamation No. 1274/2022.


ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ በአዋጁ የተጠቀሱት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

፫. **ክፍያ**

፩/ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠትና ተያያዥነት ላላቸው አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ "፩" በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፪/ ለተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያ፣ መመዝገቢያና ተያያዥነት ላላቸው አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ "፪" በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፫/ የንግድ የመንገድ የህዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት እና ተያያዥነት ላላቸው አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ "፫" በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፬/ የንግድ የመንገድ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት እና ተያያዥነት ላላቸው አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ "፬" በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፭/ ከባቡር ኦፕሬተር ፈቃድ አሰጣጥ እና ተያያዥነት ላላቸው አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ "፭" በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፮/ ሌሎች በሚኒስቴሩ የሚሰጡ አገልግሎች የሚጠየቀው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ "፮" በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

2/ The definitions given in the Proclamation shall also apply to this Regulation.

3. **Service fees**

1/ Fees to be charged for the issuance of Driver's Qualification Certificatin License and related services shall be as prescribed in the Schedule "1" attached to this Regulation.

2/ Fees to be charged for Identification, inspection, registration of Vehicles and related services shall be as priscribed in Schedule "2" attached to this Regulation.

3/ Fees to be charged for issuance of Commercial Road public Transport Operator Qualification Certificate and related services shall be as priscribed in the Schedule "3" attached to this Regulation.

4/ Fees to be charged for the issuance of Commercial Road Freight Transport Operator's Qualification Certificate and related services shall be as priscribed in the Schedule "4" attached to this Regulation.

5/ Fees to be charged for licensing of Train Operator and related services shall be as prescribed in the Schedule "5" attached to this Regulation.

6/ Fees to be charged for other Service provided by the Minister shall be as prescribed in the Schedule "6" attached to this Regulation.

፯/ ሚኒስቴሩ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ የአገልግሎት ክፍያን እንዲወስንና በየጊዜው ከወቅቱ የውጭ ምንዛሪ ጋር በማገናዘብ እንዲያሻሽል ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>ከክፍያ ነፃ መሆን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በቂ ምክንያት ሲቀርብለት ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**፭. <u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

፩/ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፶/፪ሺ፲፩ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪/ የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፮/፪ሺ፫ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፫/ የትራንስፖርት ባለስልጣን የገቢ ታሪፍ የውስጥ ደንብ ፪ሺ፬ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፬/ የዚህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፮. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺ፲፯**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

7/ The Ministry is hereby empowered to determine and ammened the fees for plate number identification timely according to the foreign exchange rate.

**4. <u>Exemption</u>**

Ministry of Finance may, for good cause, grant exemption from payment of service Fees.

**5. <u>Repealed and inapplicaable laws</u>**

1/ Driver's Qualification Certification License and related services fees Council of Ministers Regulation No.450/2019 is repealed by this Regulation.

2/ Vehicles Identification, Inspection and Registration fees Council of Ministers Regulation No.206/2011 is repealed by this Regulation.

3/ Transport Authority Revenue Tariff Internal Regulation 2012 is repealed by this Regulation.

4/ Any Regulation, Directive or practice that contradicts with this Regulation shall not be applicable to the matters covered by this Regulation.

**6. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter in to force on the date of its publication in the Federal Negarit gazette.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of May, 2025**

**ABIY AHMED (DR)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**